የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ

በመላዋ ኢትዮጵያ ከሚገኙ ጥንታውያንና ታሪካውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል በደሴቶ ጣናና በአካባቢዋ የሚገኙት ገዳማትና አድባራት ናቸው።

የጣና ሐይቅ የሚገኘው በሰሜን ኢትዮጵያ በጉጃምና በጉንደር ክፍለ ሀገር መካከል የሚገኝ በሌላው ክፍለ ሀገራት ከሚገኙ ሐይቆች ባሕሮች በስፋትም ሆነ በጥልቀት መጀመሪያውን ደረጃ ይዞ የሚገኝ ሲሆን በዓለም ከታወቀው ታላቁ የኢትዮጵያ ወንዝ የአባይ ምንጭ ነው።

የጣና ሐይቅ ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ ዋና መሥሪያ ቤቱ ባሕር ዳር ከተማ የሆነ ናሺጋ ጣና የተባለ የባሕር ትራንስፖርት ድርጅት በሳምንት መጠነኛ የሆኑ የሞተር ጀልባዎች አዘጋጅቶ ከባሕር ዳር ዘጌ ፣ ደቅ ፣ ጐርጐራ ፣ ቁንዝላ ፣ ደልጊ ከተባሉ ሥፍራዎች ሰውም ሆነ ማንኛውም የንግድ ዕቃና ጥራ ጥሬ በባሕሩ ላይ በማጓጓዝ ከፍ ያለ አገልግሎት ይሰጣል።



ባለ አራት ማዕዘን (ባለሲንሳ) የጣና ቂርቆስ ቤ ክርስቲያን

የጣና ባሕር አካባቢ በሙሉ እጅግ በጣም ለም መሬት ከመሆኑ የተነሣ ለከብት ርባታም ሆነ ለማንኛውም የእርሻ ሰብል በጣም ተስማሚ የሆነ የአየር ጠባይ ስላለው ደንብያ ፣ ፎገራ ፣ እስቴ ጣቁሳ ፣ አቸፈር ፣ ባሕር ዳርና ዘጌ ከተባሉት ሥፍራዎች የሚኖሩ ኅብረተሰቦች በሙሉ ኀሩም በሆነ ሁኔታ ከብት የሚያረቡና ጤፍ ፣ ማሽላ ፣ ሽንብራ ፣ ኑግና ሱፍ በማምረት የሚኖሩ በጣም ሀብታም የሆኑ ገበሬዎች ናቸው ይህም በመሆኑ ወደእንዚህ አካባቢ የሄደ ማንኛውም ሰው መስተንግዶው ፣ ወተት ፣ እርጎ ፣ እንጀራ በአይብ ፣ ተፈትፍቶ ይሰጠዋል። ከወተቱ ብዛት የተነሣም አንዳንድ ሰው ይቅርና እንቱ ተፈልቶ አይበው ከወጣ በኋላ እንቱ በገንዳ ተደርጎ ለከብቶች ይሰጣል። የጣና ሐይቅ ዳሩም ሆነ ውስጡ በተፈጥሮ ፀጋ የታደለ በመሆኑ ውስጡን ቢዳስሱት ዓሣ እንጂ አሸዋ የማይገኝበት ሐይቅ ነው።

የጣና ባሕር በተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን በሰው ሠራሽ ነገርም ጥሩ በመሆኑ በውስጡ በሚገኙ ደሴቶችና አካባቢው ቅዱሳት ገዳማትና አድባራት ይገኛሉ።
እነርሱም በደሴቱ ጣና ውስጥ፦

1/ ዳጋ እስጢፋኖስ 2ኛ/ ናርጋ ሥላሴ ፣ 3ኛ/ ደቅ አርሴማ ፣ 4ኛ/ ክብራን ገብርኤል 5ኛ/ ገሊላ አቡነ ዘካርያስ ፣ 6/ እንጦራ ተክለሃይማኖት ናቸው ከላይ ከጠቀስኳቸው ገዳማት ሌላ በጣና ባሕር አካባቢ የሚገኙ በጣም ጥንታውያን የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ 1ኛ/ ጣና ቂርቆስ ፣ 2ኛ/ ክርስቶስ ሠምራ ፣ 3ኛ/ ምጥራሔ ፋሲለደስ ፣ 4ኛ/ ጐርጐራ ደብረሲና ማርያም ፣ 5ኛ/ መንዳባ አቡነ አሳይ ፣ 6ኛ/ በዘጌ ውስጥ ውራ ኪዳነ ምሀረት ፣ አባ በትረ ማርያም ፉጋንዳ ተክለ ሃይማኖት ባሕር ዳር ጊዮርጊስ የሚባሉ ጥንታውያን ገዳማትና አድባራት ናቸው ከዚህ ሌላ በጣም ጥንታዊነት የሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት በጣና ባሕር አካባቢ በብዛት ይገኛሉ። ከላይ ስማቸው በዝርዝር የተገለጹት ገዳማትና አድባራት ግን ከግራኝ መሐመድ ወረራ በፊት የተተከሉና የገዳም ማኅበራዊ ኑሮ የተመሠረተባቸው ብዙ ሰባኪያን ወንጌል የወጡባቸው የልዩ ልዩ ቅዱሳን አፅም ያረፈባቸው ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሃይማኖት መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ቅዱሳት ገዳማትና አድባራት በመሆናቸውና በአሁኑ ጊዜም ቢሆን በዓለም ታሪክ ዘንድ ከፍተኛ ሥፍራ ይዘው የሚገኙ ቅዱሳት መጻሕፍትና ልዩ ልዩ ቅርሳ ቅርሶች በብዛት ተከማችተው የሚገኙባቸው ስለሆኑና ለአገራችን ከፍተኛ የሆነ የቱሪዝም ገቢ የሚያስገኙ በመሆናቸው ከሌሎቹ ለይቼ በማቅረብ እንደባሕር ውሃ ተቀድቶ ከማያልቀው ታሪካቸው የማውቀውን ያህል በጭልፋ ጨልፌ ለአንባብያን አቀርባለሁ።

ያለ አባት ልጅ አይወለድምና የነዚህ ጥንታዊያን ገዳማትና አድባራት ወላጅ አባት ስለሆነውና ለእነዚህ ቅዱሳት ሥፍራዎች መመሥረትና መስፋት ምክንያት ስለሆነው ስለጣና ቂርቆስ ከቦታው ድረስ በመሄድ ያገኘሁትንና ያጋጠሙኝን ሁሉ ለአንባብያን ባቀርብ ደስ ይለኛል።

1/ በተቀማጠሉ ብራናዎች የነቢያት ፣ የሐዋርያት ፣ የጻድቃን ፣ የሰማዕታት ሥዕል የተሳለበት የሚዘረጋና የሚተጣጠፍ በጥንታዊ የሐረግ አጣጣል ያሸበረቀ ሥዕል





www.ethiopianorthodox.org

እድጓና

2/ በየተአምሩ ሥዕል ያላት ተአምረ ማርያም

3/ በጣም ጥንታዊ የሆነ የመጾብ መስቀል

4/ ሁለት በጣም ጥንታውያን የሆኑ በትረ መስቀሎች



በጣና ቂርቆስ የሚገኝ ጥንታዊ የመጾብ መስቀል

5/ መጠንኛ የሆኑ ሥዕለ አድኅኖች

6/ በጐንደር ዘመን መንግሥት መጀመሪያ አካባቢ የተሳለ ፍትሐንገሥት

7/ የዜማው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በእጁ የጻፈው ነው እየተባለ የሚነገርለት የዜማው ምልክት የሌለው ድጓ

8/ በየዕለቱ ለንበቱና በየወር በዓላቱ የሚገለገሉባቸው ጥቂት መጻሕፍትና አልባሳት በቀለ ገበዙ እማካይነት ወጥተውልኝ በዓይኔ አይቼ ፎቶግራፍ ለማንሳት ችያለሁ።

1ኛ/ ከላይ በጠቀስኳቸው መጻሕፍቶች መካከል በአጭሩ ሳልገልፀው የማላልፈው ጉዳይ አለ ይኸም በቅዱስ ያሬድ እጅ ተጽፈ ስለሚባለው ድጓ ነው። በታሪክ እንደሚታወቀው ሁሉ ቅዱስ ያሬድ የነበረው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት ነው የጣና ቂርቆስ ገዳም ግን የተመሠረተው በአፄ ዐምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት በ14ኛ መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በተባሉ ጻድቅ ለመሆኑ ዶክተር ታደሰ ተአምራት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ፕሮፌሰር ቸርች ኤንድስቴት በተባለው መጽሐፋቸው በሚገባ ገልፀውታል። የዚህ መጽሐፈ ድጓ ሥነ ጽሁፍም ሆነ የብራናው ጠቅላላ ይዘት በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተጻፉት መጻሕፍት ምንም ዓይነት ልዩነት የለውም ነገር ግን ምልክት የሌለው በመሆኑ የያሬድ ድጓ ሊሆን አይችልም እውነቱ ግን የኢትዮጵያ ሊቃውንት እንደሚተርኩት የቀድሞ ድጓ ምልክት አልነበረውም ለሚባለው ታሪክ የጣና ቂርቆስ ድጓ እንደምስክርነት ሊቀርብ ይችላል።

2ኛ/ እዚያው በሰንበቴ ቤት ሰሞን ቤተ ክርስቲያንና አካባቢውን እየተዘዋወርኩኝ እመለከት ነበር ስለዚህ ቤተክርስቲያኑ የግር ክፍን ያለው በአራት መንገድ በተቀረፀ በጥርብ ድንጋይ የተገነባ ሲሆን በተለይ የቤተ መቅደሱ ህንፃ ግን ቀይ ሸክላ በመሳሰሉት ድንጋዮች የታነፀው በዚያ ዓይነት ድንጋይ በጣና ቂርቆስ አካባቢ አይገኝም ነገር ግን ከየት እንደመጣ ብጠይቅ የሚያስረዳኝ ሰው አላገኘሁም ከቤተ ክርስቲያኑ በስተደቡብ በኩል አንድ አለት አለ በዚህ አለት ላይ ሁለት መጠነኛ የሆኑ ከአለት የተፈለፈሉ ጉድጓዶች አሉ። እነዚህ ጉድጓዶች የቀይና የጥቁር ቀለም መበጥበጫና ማቡኪያ ነበሩ ብለው ተርከውልኛል።

4ኛ/ በዚህ አካባቢ በአለት ላይ የተተከለች በጣም ጥንታዊት የሆነች የብረት መስቀል አለች ካህናቱ እንደሚሉት ከሆነ ይህ መስቀል የአቡነ ሰላማ ነበር ይላሉ። ይህ መስቀል በዘመናችን አንድ ተአምር ፈጽሞ አል ተአምሩም አንድ መነኩሴ ከትግራይ ክፍለ ሀገር ወደጣና ቂርቆስ ይመጣና ይቀመጣል በዚህ ጊዜ ይህ መስቀል የአቡነ ሰላማ ነው የሚል ታሪክ ከካህናቱ ይሰማል እንግዲያማ አባ ሰላማ አገራቸው ትግሬ ነው ስለዚህ ይህን መስቀል እዚህ ማን አመጣው ይልና በሌሊት ሰርቆ ይጠፋል። ነገር ግን መነኩሴው ይህን መስቀል ይዞ የገር ለሀገር ሲንከራተት ከኖረ በኋላ በዓመቱ ይዞት ወደ ጣና ቂርቆስ መጣና በሕዝቡ ፊት ቆሞ እንዲህ ሲል ተናገረ ይህን መስቀል ከወሰድኩበት ቀን ጀምሮ የቀን ዕረፍትና የሌሊት እንቅልፍ አላገኘሁም እንዲያውም ሌሊት በሕልሜ አንድ ሰው እየመጣ ይህን መስቀል ካመጣህበት መልስ እያለ ስለአስቸገረኝ ይዤው መጥቻለሁ ሲል በሕዝብ ፊት ተናዘዘ። አሁን ጊዜ መስቀሉ በቦታው ይገኛል።

5ኛ/ ከዚህ ሌላ ከጣና ቂርቆስ በስተሰሜን አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ ከባሕሩ ጫፍ ላይ ኃጢአተኛና ጻድቅ የሚለይባትና የምትባል ቀዳዳ ድንጋይ አለች። ይህች ቀዳዳ ድንጋይ ሾልኮ ያለፈ ሰው ፍጹም ጻድቅ ነው ተብሎ የሚታመንበት ሲሆን ቀዳዳዋን ሳይሾልክ የቀረ ሰው ግን እንደ ኃጢአተኛ ይቆጠራል ከዚህም እምነት የተነሣ በቂርቆስ ዓመት በዓልና በኅንቦት 12 ቀን የክርስቶስ ሠምራን በዓል ለማክበር የመ



www.ethiopianorthodox.org

ማው ሕዝብ በጠቅላላ ይህችን ቀዳዳ ሳይሞክር እያሄደም የሾለኩት ሲደሰቱ ያልሾለኩት ደግሞ እየደጋገሙ ከደንጋይ ጋራ ሲታገሉ ይውላሉ ።

ጣና ቂርቆስ የቅዱሳት መጻሕፍትና የጥንታውያን ቅርጻ ቅርሶች መጋዘን ነው እየተባለ ቢነገርለትም ከቦታው ድረስ በመሄድ ያገኘሁት መልስ ከሩቅ ሆኖ ተቀብሬ ሆል የሚል መልስ ቢሰጠኝም ከመሬት በታች ያለውን ውሸት ሳይሆን ከመሬት በላይ ያለውን እውነት ተመልክቼ ቀዳዳዋን ደንጋይ ሾልኬ ተመልሼአለሁ ።

ይቀጥላል ።

ገርማ ሒልያስ